# የጉራፈረዳ ነዋሪዎች በግድያ እና ዝርፍያ እየተሰቃዩ መሆኑን ገለፁ

By **እዮብ ውብነህ** - 21/03/2022



ሰኞ መጋቢት 12 ቀን 2014 (አዲስ ማለዳ) በቤንች ሸኮ ዞን ጉራፈርዳ ወረዳ ግድያ እና ዝርፍያ ህዝቡን ምሬት ውስጥ መክተቱ ተገለፀ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ማንነታቸው ያልታወቁና በቡድን በሚንቀሳቀሱ ታጠቂዎች ተደጋጋሚ ትንኮሳ፣ የከብትና የጦር መሳሪያ ዝርፊያ እየተፈጸመ እንደሚገኝ ስማቸውን መጥቀስ ያልፈለጉ የአካባቢው ነዋሪዎች ለኢትዮ ኤፍ ኤም ተናግረዋል።

በቤንች ሸኮ ዞን ጉራ ፈርዳ ወረዳ ካሉ ስድስት ቀበሌዎች ውስጥ አንዱ በሆነው ኩጃ ቀበሌ ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተደጋጋሚ የከብት ዝርፊያ እንዲሁም በነዋሪዎች ላይ ግድያ እየተፈጸመ መሆኑን የቀበሌው ነዋሪ የሆነው ግለሰብ ተናግሯል።

ስለጉዳዩ የሬዲዮ ጣቢያው የጠየቃቸው የቤንች ሸኮ ዞን የመንግስት ኮሚኒኬሽን መመርያ ኃላፊ ተስፋይ ጊስካር፤ ለጸጥታው መደፍረስ በዋናነት በቀበሌዋ ከፍተኛ የሆነ ህገ ወጥ ጦር መሳሪያ ዝውውርና ሽያጭ መበራከት ዋናው ምክንያት ነው ያሉ ሲሆን፤ እንዲህ ያለውን ድርጊት ህብረተሰቡ በአንድነት አለመታገሉ ደግሞ ሌላው ምክንያት ነው ብለዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ማንነታቸው ያልታወቁና ታጥቀው በቡድን በሚንቀሳቀሱ አካላት ተደጋጋሚ የከብትና የጦር መሳሪያ ዝርፊያ እየተካሄዴ ሲሆን ንጹሀን ላይ ደግሞ ግድያ እየተፈፀመ ነው ሲሊ ተስፋይ አረጋግጠዋል።

ቀበሌዋ ለጋምቤላ ክልል አኙዋክ ዞን ዲማ ወረዳና ምዕራብ ኦሞ ዞን አዋሳኝ በመሆኗ ከዚህ ቀደም ከሱርማ ወረዳ አካባቢ ተነስተው በሚመጡ ሽፍቶች የከብት ዝርፊያ ይፈጸም እንደነበር ተናግረዋል።

አሁንም ያለው ከዚሁ ጋር የተያያዘ እንደሆነ የተናገሩት ኃላፊው፤ ዝርፍያው እና ግድያው የሚፈጸመው ጨለማን ተገን አድርገው በሚንቀሳቀሱና በጫካ የሚደበቁ ሰርጎ ገብ ታጣቂዎች እንደሆነ ገልፀዋል።

---

**ተጨማሪ ጽሑፎች:**

- ሕገ ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውር
- ተፈናቃዮች ማግኘት የሚገባቸውን እያገኙ ይሆን?
- እናትና አባት ተገድለው ልጅ መውሰድ ማለት፣ ይሄ ዘር ማጥፋት ነው

---

በትላንትናው ዕለትም በጒራ ፈርዳ አንድ ግለሰብ በሽፍቶች እንደተገደለ እና ከብቶቹም እንደተዘረፉበት ነው ተስፋዬ የተናገሩት።

አሁን በኩጃ ቀበሌ ለሚታየው የጸጥታ መደፍረስ ህብረተሰቡና የወረዳው ጸጥታና ፖሊስ መዋቅር ወንጀልን በጋራ ለመከላከል የሚያደርገው ቅንጅት አናሳነት ተጠቃሽ ምክንያት መሆኑን ተናግረዋል።

ህብረተሰቡ በጒያው የተመሸጉ ህገ ወጥ ጦር መሳሪያ ነጋዴዎች ፣ ዱላላዎችና አስተላላፊዎችን ለህግ አካላት አሳልፎ እስካልሰጠና ተደራጅቶ ወንጀልን እስካልተከላከለ ድረስ መሰል የጸጥታ ችግሮች በፖሊስና በጸጥታ መዋቅሩ ሥራ ብቻ የሚፈቱ አይሆኑም ብለዋል።

በቀጠናው ከፍተኛ የጦር መሳሪያና የጥይት ፍሬ ዝውውርና ሽያጭ የሚፈጸምበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ችግሩን አሳሳቢ እንዳደረገው ኃላፊው ገልጸው፤ የወረዳው የጸጥታ መዋቅሮች ችግሩን ለመፍታት ከህዝቡ ጋር እየመከርንበት እንገኛለን ሲሉም ለሬዲዮ ጣቢያው ተናግረዋል።

______________________

ትክክለኛውን የአዲስ ማለዳ ሶሻል ሚዲያ በመቀላቀል ቤተሰብ ይሁኑ

Telegram ➲ t.ly/SOXU

Facebook ➲ t.ly/flx8

YouTube ➲ t.ly/vSgS

Twitter ➲ t.ly/mxA4n

---

**እዮብ ውብነህ**


## ስለ እኛ

አዲስ ማለዳ ወቅታዊ የአገራችንን ጉዳዮች በስፋትና በጥልቀት የምትተነትን፣ እንዲሁም የተረጋገጡና የትም ያልተሰሙ ዜናዎች የሚቀርቡባት የብዙኃን መገናኛ ናት። በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚዲያ ባለስልጣን በመዝገብ ቁጥር 241/2010 ተመዝግባለች።

ያግኙን: info@addismaleda.com

## ይከታተሉን